# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# ተወዳጅ ልጅ ባሪያ ሆነ


ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus
ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): M. Kerr; Sarah S; Alastair P.
የተተረጎመው: Eyerusalem Dechasa
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada



©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ይስሃቅ ልጁ ያዕቆብ ቤት ስለነበር በጣም ደስተኛ ነበር። ዔሳው እንኳን በአንድ ወቅት ለመግደል ምሎ የነበረውን ወንድም ተቀብሎታል። ነገር ግን የያዕቆብ ልጆች ደስታኛ አልነበሩም ምክንያቱም ታናሽ ወንድማቸው ዮሴፍ በአባታቸው ተወዳጅ ነበርና።



የዮሴፍ ወንድሞች ሕልሙን ሲነግራቸው ይበልጥ ተበሳጩ። "የእኔ የእህል ነዶ ከፍ ብሎ ቆመ እናም የወንድሞቼ ነዶዎች ሰገዱለት" አላቸው። ይህ ሕልም ዮሴፍ ከወንድሞቹ የበለጠ አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው።



3

በዮሴፍ ሁለተኛ ሕልም ላይ ፀሐይ, ጨረቃና ከዋክብቶች ለእሱ ሰገዱለት። አባቱ ያዕቆብ እንኳ ራሱን ከወላጆቹና ከወንድሞቹ በላይ ስላደረገ ተበሳጨ።



4

አንድ ቀን ያዕቆብ ዮሴፍን ወንድሞቹ መንጎቻቸውን ወደሚጠብቁበት ወደ እርሻው ቦታ ላከው። ወንድሞቹ ሲመጣ አዩት። "ህልመኛውን እንግደለው!" ብለው አጉረመረሙ። ዮሴፍ በእሱ ፊት ያለውን አደጋ አላውቅም ነበር።



5

ሮቤል ታላቅ ወንድሙ አልተስማማም። "ደም ማፍሰስ የለብንም" አለ። "ተመልከቱ, እዚህ ጉድጓድ አለ እዚህ እንዲሞት እንጣለው" ብሎ ሀሳብ አቀረበ። ሮቤል በሌሊት መጥቶ ዮሴፍን ለማዳን አቅዶ ነበር።



6

ዮሴፍ በደረሰ ጊዜ ወንድሞቹ ያዙትና ያዕቆብ ለተወዳጅ ልጁ የሰራለትን በቀለማት ያጌጠችውን ቀሚስ አወለቁበት። ከዚያም ወደ አስከፊው ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት።



7

ሮቤልም ዝም ብሎ ነበር። ብዛት ያላቸው ግመሎች ወደ ግብፅ በመጉዝ ላይ ነበሩ። ይሁዳም ወንድሞቹን "ዮሴፍን እንሸጠው" በማለት ጨኸ። እነሱም ተስማሙና ዮሴፍን በሀያ ብር ብር ሸጡት።



8


ዮሴፍም የሚረዳው ሰው ሳይኖር ከቤተሰቦቹና ከትውልድ ሀገሩ
ሲወስዱት ሲያይ እጅግ ፈራ።
9


"ይህ የዮሴፍ ልብስ
ነው? በደም
ተጨማልቆ በበረሃ
ውስጥ አገኘን" ጨካኝ
ወንድሞች ለያዕቆብ
የሚወደው ልጁ
በአውሬ እንደተበላ
እንዲያምን አደረጉት።
ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ
እና አለቀሰ። ማንም
ሊያጽናናው የሚችል
አልነበረም።
10


በግብጽ ዮሴፍ በፍርሃት
እና በብቸኝነት ውስጥ
ነበር። ምናልባት ወደ
ቤቱ ይጓዝ ይሆናል ግን
ማምለጥ አልቻለም።
እርሱ በግብፃዊው
በጲጥፋራ ቤት ውስጥ
ባሪያ ነበር። ጲጥፋራ
ዮሴፍ ምንጊዜም
ጠንክሮ እንደሚሠራና
ሊታመን እንደሚችል
ተገነዘበ።
11


"የምትሰራው ሁሉ ወደ መልካም
ይለወጣል" ጲጥፋራ አንድ ቀን ለዮሴፍ
ነገረው። "እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው"
ዋነኛ አገልጋዬ "እንድትሆን ፈልጋለሁ
በጉዳዮቼ እና በአገልጋዮቼ ሁሉ ላይ
አለቃ እንድትሆን ፈልጋለሁ" አለው።
12


እግዚአብሔርም በዮሴፍ
ምክንያት ለጲጢፋራ መልካም
ምርት እና ሀብት ሰጠው።
ዮሴፍ ትልቅ ቦታ ያለው
ሰው ቢሆንም አሁንም
እግዚአብሔርን በታማኝነት
ማገልገል ጀመረ። ይሁን እንጂ
ዮሴፍ ችግር አጋጠመው።
13


የጲጥፋራ ሚስት መጥፎ ሴት ነበረች። ዮሴፍ የባሏን ቦታ
እንዲወስድ ጠየቀችው። ዮሴፍ ግን ፈቃደኛ አልሆነም።
ጲጥፋራን በመበደል እግዚአብሔርን አልበድልም አለ። ሴቲቱ
ልታስገድደው ስትሞክር ሮጠ
አመለጣት። ነገር ግን
ልብሱንይዛ ጨኸች።
14

"ባሪያህ ነካኝ" የጲጥፋራ ሚስት አጉረመረመች። "ተመልከት ፥ ይኸው ልብሱ" ብላ አሳየችው። ጲጥፋራ ተቆጣ። ምናልባት ሚስቱ ውሸታም መሆኗን ያውቅ ይሆናል። ነገር ግን አንድ ነገር ማድረግ ነበረበት። ታዲያ ምን ያደርግ ይሆን?



15

ጲጥፋራ ዮሴፍን እስር ቤት አስገባው። ዮሴፍ ምንም ስህተት ባይኖርበትም መራራም ሆነ ቁጡ አልነበረም። ምናልባትም ካለፉት ችግሮቹ ተምሮ ይሆናል። እርሱ የትም ቦታ ቢሆንም እግዚአብሔርን ካከበረ እስር ቤት ውስጥ እንኳን ቢሆን እግዚአብሔር ደግሞ እሱን ያከብረዋል።



16

ተወዳጅ ልጅ ባሪያ ሆነ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ኦሪት ዘፍጥረት 37; ዘፍጥረት 39

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

17

# መጨረሻ

7 60

18

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16

19